የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ዋና ኦዲተር መሥሪያ ቤት
THE FEDERAL DEMOCRATIC
REPUBLIC OF ETHIOPIA
OFFICE OF THE FEDERAL
AUDITOR GENERAL

ቁጥር OFAGF-03.9/1/34
ቀን 13/04/2015

ለተከበሩ አቶ ተፈሪ ፍቅሬ

የጠቅላይ ሚኒስቴር ጽ/ቤት ኃላፊና የካቢኔ ጉዳዮች ሚኒስትር

ለተከበሩ አቶ ሰለሞን ሶካ

የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት አስተዳደር ዋና ዳይሬክተር

አዲስ አበባ

ጉዳዩ፡- የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት አስተዳደር የ2014 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ውጤትና አስተያየትን ይመለከታል

በርዕሱ የተጠቀሰውን የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት አስተዳደር የ2014 በጀት ዓመት የኦዲት ውጤትና አስተያየት የያዘ 17 ገጽ የኦዲት ሪፖርት እና 25 ገጽ የሂሳብ ሪፖርቶች በድምሩ 42 ገጽ የያዘ ከዚህ ደብዳቤ ጋር አያይዘን የላክን መሆኑን እንገልፃለን፡፡

ከማክበር ሰላምታ ጋር

አበራ ታደሰ
የፌዴራል ም/ዋና ኦዲተር

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት አስተዳደር
የ2014 በጀት ዓመት ሂሣብ ኦዲት ሪፖርት

ታህሳስ /2015

አዲስ አበባ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት አስተዳደር
የ2014 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ሪፖርት

የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት አስተዳደር የተመደበለትን የመደበኛና የካፒታል ሂሳብ በጀት ለታቀደለት ዓላማ ማዋሉን፣ እንዲሁም ሂሳቡ በመንግሥት የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መሠረት መያዙንና የመንግሥት ሀብትና ንብረት በሚገባ መጠበቁን ለማረጋገጥ የ2014 በጀት ዓመት ሂሳብ ሪፖርቶችን እና የሂሳብ ማስታወሻዎችን ኦዲት አድርገናል፡፡

የሂሳብ ሪፖርቶችን የማዘጋጀት ኃላፊነት የአስተዳደር ሥራ አመራር ሲሆን፣ የሂሳብ ሪፖርቶችን ኦዲት በማድረግ ሙያዊ የኦዲት አስተያየት መስጠት ደግሞ የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ኃላፊነት ነው::

ኦዲቱ የተከናወነው የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤትን ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 982/2008 ለመ/ቤታችን በተሰጠው ሥልጣን ሲሆን፣ ዓለም አቀፍ የኦዲት ደረጃዎችን (ISSAI) መሠረት በማድረግ ነው፡፡ እነዚህን የኦዲት ደረጃዎች መከተል ኦዲቱን በሚገባ አቅደን በመሥራት በተዘጋጁት የሂሳብ ሪፖርቶች ላይ አጥጋቢ የሆነ የኦዲት አስተያየት ለመስጠት ያስችለናል፡፡ ኦዲታችን ፡-

- በሂሳብ ሪፖርቶች ላይ የሰፈሩትን አሀዞችና መግለጫዎችን የሚደግፉ ማስረጃዎችን በናሙና ኦዲት ማከናወንን፣
- የሥራ አመራሩ የሂሳብ ሪፖርቶችን ሲያዘጋጅ ያደረገውን ጉልህ ግምቶች እና ውሳኔዎችን መመዘንን፣
- የሂሳብ አያያዝ ፖሊሲዎች ከዓመት ዓመት ሳይቀያየሩ በሥራ ላይ መዋላቸውን እና በበቂ ሁኔታ መገለጻቸውን ማመዛዘንን ያጠቃልላል፡፡

ከዚህም በተጨማሪ የተዘጋጁት የሂሳብ ሪፖርቶች ተገቢ የሆኑ አዋጆች፣ ደንቦችና በተከታታይ የወጡ መመሪያዎችን በመከተል የተዘጋጁ መሆኑን በናሙና ኦዲት ማከናወንን ይጨምራል::

የሂሳብ ሪፖርቶች ጉልህ ከሆኑ ስህተቶች የፀዱ ለመሆኑ በቂ ማስረጃና አጥጋቢ ማረጋገጫ የሚሰጥ መረጃና ማብራሪያ ሊያስገኝ በሚችል መልኩ ኦዲቱን አቅደን አከናውነናል፡፡

ለኦዲቱ ሥራ መሠረት የሆኑት አስተዳደር ያቀረባቸው የሂሳብ ሪፖርቶች፣ መዛግብት፣ ደጋፊ ማስረጃዎች፣ እንዲሁም በኦዲት ተደራጊው መ/ቤት ሥራ አመራር የተሰጡ

ማብራሪያዎች ናቸው:: ኦዲቱ የተከናወነው የበጀት ዓመቱን የሂሳብ እንቅስቃሴ ሊወክሉ የሚችሉ ናሙናዎችን በመውሰድ በጥልቀትና በዝርዝር ኦዲት በማድረግ ነው::

የሚከተሉት የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት አስተዳደር የሂሳብ ሪፖርቶች ከዚህ የኦዲት ሪፖርት ጋር ተያይዘው ቀርበዋል::

- የገቢ/የዕርዳታ/የብድር ሂሳብ ሪፖርት፣
- የወጪ ሂሳብ ሪፖርት፣
- የተሰብሳቢ ሂሳቦች ሪፖርት፣
- የተከፋይ ሂሳቦች ሪፖርት፣
- የዝውውር ሂሳብ ሪፖርት፣
- የሂሳብ ሚዛን ሙከራ፣

ከዚህ የኦዲት ሪፖርት ጋር ተያይዘው ቀርበዋል፡፡

ለኦዲት አስተያየቱ መሰረት የሆኑት ጉዳዮች፣

የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት አስተዳደር የሂሳብ ሪፖርቶች ጉልህ የሆነ ግድፈት የሌለባቸው፣ በአዋጅ በተፈቀደው በጀት እና በመንግሥት ሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መሠረት የተዘጋጁ እና የተሰበሰበው ገቢ፣ የተከፈለው ወጪና የበጀት አጠቃቀሙ የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅን፣ ደንብና መመሪያን የጠበቁ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣

1. <u>በገቢ እና በወጪ መታየት የነበረበት በተከፋይ ሂሳብ የተመዘገበ ስለመሆኑ፤፤</u>
   የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት ኤጀንሲን እንደገና ለማቋቋም የወጣ አዋጅ ቁጥር 808/2006 አንቀጽ ስድስት ንዑስ አንቀጽ 15 ህገራዊ አቅም ባልተፈጠረባቸው ክፍተቶች ደህንነታቸው የተጠበቁ የኢንፎርሜሽን ማኔጅመንት መሰረት ልማቶችን እና ስርዓቶችን የማበልጸግና የመዘርጋት፣ እንዲሁም ለሚያቀርበው ምርትና አገልግሎት ተመጣጣኝ ክፍያ ማስከፈል እንደሚችል ይደነግጋል፤ እንዲሁም የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት ኤጀንሲን እንደገና ለማቋቋም በወጣ አዋጅን ለማስፈጸም የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 320/2006 ክፍል ሦስት አንቀጽ 14 ስለፕሮጀክት አስተዳደር አርዕስት ንኡስ አንቀጽ 1 ኤጀንሲው የራሱ የፕሮጀክት ሂሳብ አወቃቀር ይኖረዋል በማለት ይደነግጋል፡፡ አስተዳደሩ በአዋጁ መሰረት ተግባራዊ እያደረገ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡-

   - አስተዳደሩ አቅም ባልተፈጠረባቸው ክፍተቶች ደህንነታቸው የተጠበቁ የኢንፎርሜሽን ማኔጅመንት መሰረተ ልማቶችን እና ስርዓቶችን የማበልጸግና የመዘርጋት ሥራ ለማከናወን ከተለያዩ ድርጅቶች ገቢ የሚሰበስብ ቢሆንም በደንቡ መሰረት ለፕሮጀክቱ ራሱን የቻለ የሂሳብ አወቃቀር በማዘጋጀት ወይም የመደበኛው ሂሳብ ትክክለኛውን ምዝገባ በማከናወን ሪፖርት ማድረግ ሲገባው በገቢ ብር 209,797,389.18 እና በበጀት ዓመቱ የወጣው ወጪ ብር 359,341,792.79 ከመደበኛ በጀት ሂሳብ ላይ በተከፋይ ሂሳብ 5054 ምዝገባ የሚሰራ በመሆኑ በሂሳብ እንቅስቃሴ መዝገብ ላይ በገቢና በወጪ ያልተመዘገበና በሂሳብ ሪፖርት ላይ የማይታይ መሆኑ፤
   - አስተዳደሩ ለ21 ድርጅቶች የተለያዩ ስራዎችን ለማከናወን ውል በገባው መሰረት ከድርጅቶቹ ሥራውን ለማከናወን ከተቀበለው ገንዘብ በላይ ስራውን ለማከናወን ያወጣው ወጪ በብልጫ ብር 26,661,908.99 ወጪ ያደረገ

በመሆኑ በድርጅቶች ስም በ5054 በተመዘገበው ተቀጽላ ሌጀር ላይ ባልተለመደ ሚዛን /ዴቢት የታየ መሆኑ፤

2. <u>ያለአግባብ የተመዘገበ የገቢና ተጨማሪ እሴት ታክስ ሂሳብ በተመለከተ፤</u>

ተጨማሪ እሴት ታክስ ተመላሽ ስለሚደረግበት ሁኔታ ለመወሰን የወጣ መመሪያ ቁጥር 148/2011 አንቀጽ 2 ንኡስ አንቀጽ 7 ታክስ ማቀናነስ ማለት ታክስ ከፋዩ ዕቃ ወይም አገልግሎት ሲገዛ የከፈለውን ተጨማሪ እሴት ታክስ ዕቃዉን በሚሸጥበት ጊዜ ከሚሰበስበው ተጨማሪ እሴት ታክስ በመቀነስ ቀሪውን ለታክስ ባስልጣኑ ገቢ የሚያደርግበት ወይም በአብላጫ የተከፈለ ተጨማሪ እሴት ታክስ ለሌሎች የታክስ ወይም የቀረጥ ዕዳዎች ማካካሻ እንዲውል እንደሚያደርግና ፌደራል መንግሥት ሂሳብ አያያዝ ሥርዓት የተጨማሪ እሴት ታክስ መያዣ የሀገር ውስጥ ገቢ ባለስልጣን ተጨማሪ እሴት ታክስ ክፍያዎች ሲሰበስብ ከተሰበሰበው ውስጥ ከፊሉ በግብር ከፋዩ ሊጠየቅ እና ሊመለስ ይችላል፡፡ ይህ ሊመለስ የሚችል የገንዘብ መጠን የመያዣ ገንዘቡ በሚሰበሰብበት ጊዜ በተከፋይ ተጨማሪ እሴት ታክስ ሂሳብ መደብ 5058 መመዝገብ እንዳለበት ይገልጻል፡፡

በተጨማሪም የታክስ ደረሰኝ አጠቃቀም እና አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 149/2011 ዓ.ም ክፍል ሰባት ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች አንቀጽ 27 ለመንግሥት ባለበጀት መ/ቤት እና መንግሥታዊ ላልሆኑ ድርጅቶች የደረሰኝ ህትመት ፈቃድ አሰጣጥ ን/አ 1 የመንግሥት ባለበጀት መስሪያ ቤቶች ለሻጩ ከሚከፈል ሂሳብ ላይ ቀንሰው ለሚያስቀሩት የተጨማሪ እሴት ታክስ የሚሰጡት ደረሰኝ የታክስ ባለስልጣኑን በማስፈቀድ ማሳተም ያለባቸው ሲሆን ሌሎች ደረሰኞች በገንዘብ ሚኒስቴር ወይም በክልል እና ከተማ አስተዳደር ፋይናንስ ቢሮዎች የሚፈቀድ እንደሆነ ይገልጻል፡፡ አስተዳደሩ በመመሪያው መሰረት ተግባራዊ እያደረገ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡-

- በመመሪያው እንደተገለጸው ተጨማሪ እሴት ታክስ ተቀንሶ የሚቀርባቸው ለትርፍ ከተቋቋሙ ድርጅቶች ሲሆን አስተዳደሩ ለትርፍ ያልተቋቋመ እና ንግድ ፈቃድ የሌለው ቢሆንም መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች የተጨማሪ እሴት ታክስ ከአስተዳደሩ ጋር ውል ካላቸው መ/ቤቶች (ድርጅቶች) ቀንሰው ያስቀሩትን ሂሳብ ብር 19,345,842.02 በሂሳብ መደብ 5058 /ተመላሽ

ተጨማሪ እሴት ታክስ/ በዕዳ የተመዘገበና በሂሳብ ሪፖርት ላይ በመካተቱ የተከፋይ የሂሳብ ያለአግባብ ከፍ ብሎ እንዲታይ ያደረገው መሆኑ፤

☞ በትክክለኛው የሂሳብ አመዘጋገብ ስርዓት ተከፋይ ሂሳብ በክሬዲት ሚዛን የሚታየው በመ/ቤቱ በዕዳ የተያዘና የሚከፈል ገንዘብ ሲኖር ብቻ ቢሆንም በሌላ አካል ተቀንሶ የቀረውን ተጨማሪ እሴት ታክስ ተከፋይ ሂሳብ ብሎ መመዝገብ እንዳልነበረበትና አስተዳደሩ ከድርጅቶች ገንዘብ ሲቀበል ሙሉ ክፍያው በባንክ ሂሳብ ገቢ ሳይሆን ገቢ እንደሆነ በማድረግ በገቢ ደረሰኝ ላይ ምዝገባውን ሲያከናውን፡-

የባንክ ሂሳብ/ 4103------------------------ዴቢት

ሂሳብ መደብ 5058 (ተ.እ.ታ ማቆየት የሚከፈል)------------ክሬዲት

ተከፋይ ሂሳብ መደብ 5054--------------------------------------ክሬዲት

በዚህ መሰረት በማከናወን ያልተቀበለውን ገንዘብ እንደተቀበለ በማድረግ ያለአግባብ ገቢው ከፍ ብሎ እንዲታይ ያደረገና የተከፋይ ሂሳብ መደብ 5058 ለክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች የሚሰጠውን የታክስ ክፍፍል ድርሻ ለመያዝና ለመክፍል በገቢዎች ሚኒስቴር ብቻ ምዝገባ ላይ የሚውለውን የሂሳብ መደብ ያለአግባብ እየተጠቀመ መሆኑ፡፡

- በመመሪያው መሰረት ተጨማሪ እሴት ታክስ ተቀንሶ የሚቀረው ለትርፍ ከተቋቋሙ ድርጅቶች እንደሆነ ቢገልጽም አስተዳደሩ ለትርፍ ያልተቋቋመ እና ንግድ ፈቃድ የሌለው መንግስታዊ ተቋም ሲሆን የቫት ደረሰኝ እንዲያሳትም ማን እንደፈቀደለት ለማጣራት የተፈቀደበትን ደብዳቤ ለኦዲት እንዲያቀርብ በተደጋጋሚ ቢጠየቅም ሊያቀርብ ያልቻለ መሆኑ፤
- አስተዳደሩ የሚያሳትማቸው ደረሰኞች በገንዘብ ሚኒስቴር በኩል መፈቀድ ሲኖርባቸው ፈቃድ ሳያገኝ የተጨማሪ እሴት ታክስ ደረሰኝ አሳትሞ የሚጠቀም ከመሆኑ በተጨማሪ ደረሰኞቹም ቆጠራ የማይደረግባቸው እና ማመዛዘኛ የማይሰራ መሆኑ፤

በኦዲቱ ወቅት ተረጋግጧል፡፡

3. <u>የወተት አበል ክፍያን በተመለከተ፣</u>

የሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴር በቀን 12/10/2004 ባስተላለፈው መመሪያ የወተት አበል ተፈቅዶላቸው ለነበሩ የስራ መደቦች እየተከፈለ ያለው የወተት አበል ከወቅቱ ገበያ ጋር የተመጣጠነ ባለመሆኑ ከተቋማት በተደጋጋሚ በቀረበው ጥያቄ መነሻ መሰረት ተጠንቶ ከሐምሌ 1 ቀን 2004 ዓ.ም ጀምሮ በወር ወደ ብር 80.00 ከፍ እንዲል በተፈቀደው መሰረት ክፍያዎች እየተፈፀሙ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡-

- አስተዳደሩ የወተት አበል ለሰራተኞቹ ክፍያ ሲፈጽም በመመሪያው በወር 80.00 የተፈቀደ ቢሆንም በቀን በሊትር ብር 15.56 በማድረግ ለ26 የስራ ቀን ብር 404.56 እንዲከፈል በመደረጉ ለአንድ ሰራተኛ በመመሪያ ከተፈቀደው በላይ ብር 324.56 በመክፍል በድምሩ ብር 864,950.96 ያለአግባብ ክፍያ የተፈጸመ መሆኑ በኦዲቱ ወቅት ተረጋግጧል፡፡

4. <u>ሳይፈቀድ ለውጭ ሀገር ጉዞ የተፈጸመ የትራንስፖርት ክፍያ፤</u>

ሐምሌ 2009 ዓ.ም የቀድሞ ገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ባወጣው የ2010 በጀት ዓመት ወጪ ለመቀነስ የተዘጋጀ የአዘገጃጀትና የአቀራረብ መመሪያ የመደበኛ ወጪን በተመለከተ ርዕስ ስር በተራ ቁጥር 11 የውጪ ሀገር ጉዞን በተመለከተ፡- የሚኒስቴር መ/ቤቶች በስራቸው ያሉትን የተጠሪ መ/ቤቶች ኃላፊዎች ጭምር የውጭ ሀገር ጉዞ ፕሮግራም ማለትም የፕሮግራሙ ዓላማ፤ የተሳታፊ ብዛት፤ የቆይታ ጊዜ እና ወጪን የሚያሳይ የውጭ ጉዞ ፕሮግራም በማዘጋጀት ለጠቅላይ ሚኒስቴር ጽ/ቤት ቀርቦ ሲፈቀድ ተግባራዊ ይሆናል፡፡ ከዚህ ውጭ በመካከለኛ አመራርና ባለሞያ ደረጃ የሚደረጉ የውጭ ጉዞዎች ሊያስገኝ የሚችለውን ጠቀሜታ በአግባቡ በመገምገም ለትራንስፖርት እና ለውሎ አበል የሚወጣውን ወጪ መቀነስ ያስፈልጋል፡፡ በተጨማሪም በ2011 የበጀት ቅነሳ መመሪያ አንዳንድ መ/ቤቶች በሚኒስተሮች ምክር ቤት የተሰጠውን ውሳኔ ወደ ጎን በመተው የተለመደውን አሰራር እየተከተሉ በመሆኑ የወጪ ቅነሳው አፈጻጸም አቅጣጫ ቀጣይነት ያለው መሆኑን በመገንዘብ የመ/ቤቱ የበላይ አመራር ጥብቅ በሆነ ዲሲፕሊን የወጪ ቁጠባ መመሪያ ተግባራዊ እንዲደረግ አስታውቋል፡፡ የውጪ አገር ጉዞዎችን በተላፈው መመሪያ መሰረት ለጠቅላይ ሚኒስቴር ጽ/ቤት እየጠየቀና እያስፈቀደ መሆኑን ለማረጋገጥ የውሎ አበልና ትራንስፖርት ወጪዎች ናሙና ተወስዶ ኦዲት ሲደረግ ፡-

☞ አስተዳደሩ ጠቅላይ ሚኒስቴር ጽህፈት ቤትን የውጭ ሀገር ጉዞ ጠይቆ በቀን 08/10/2014 በደብዳቤ ቁጥር መ50-887/587 ወደ ኬንያ/ናይሮቢ እንዲሄዱ ከተፈቀደላቸው ሰዎች ውጪ ወ/ሮ ሂሩት በቀለ የአውሮፕላን ትኬት የተቆረጠላቸው በመሆኑ ግለሰቧ ለምን ስራ እንደሄዱ እና የአስተዳደሩ ሰራተኛ ስለመሆናቸው ለማረጋገጥ በቀን 27/12/2014 ዓ.ም ለሰው ኃይል ልማት እና አስተዳደር ዳይሬክቶሬት የተጠየቀ ሲሆን በቀን 27/12/2014 ዓ.ም በደብዳቤ ቁጥር ኢ.መደአ9/ጀጠ3/520/14 ግለሰቧ የአስተዳደሩ ሰራተኛ አለመሆናቸውን በመረጋገጡ የአስተዳደሩ ሰራተኛ ላልሆኑና በምን ምክንያት በዚህ ጉዞ ውስጥ እንደተካተቱ የሚገልጽ ማስረጃ ሳይኖርና ጉዟቸውም በጠቅላይ ሚኒስቴር ጽ/ቤት ሳይፈቀድ የደርሶ መልስ የትራንስፖርት ወጪ እንዲሸፍን በአስተዳደሩ ዋና ዳይሩክተር በመፈቀዱ በቀን 27/10/2014 በወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 288641 በሂሳብ መደብ 6232 ብር 138,117.00 ያለአግባብ ከመመሪያ ውጪ የጉዞው ክፍያ የተፈጸመ መሆኑ፤

5. <u>ቁጠባን፣ የአፈጻጸም ብቃትን እና ውጤታማነትን ማረጋገጥያላስቻለ ግዥ በተመለከተ፤</u>

☞ አስተዳደሩ በግልጽ ጨረታ መደበኛ ማዕቀፍ 01/2014 በቀን ሐምሌ 29 2013 ዓ.ም ባወጣው ባለ 5 ኮከብ ሆቴል ከተወዳደሩት ሆቴሎች ውስጥ ጌትፋም ሆቴል በማሸነፍ በቀን 04/01/2014 ውል ያሰረ ሲሆን ውል ከገባባቸው የምግብ አይነቶች ውስጥ አንደኛ ደረጃ ብፌ የጾምና የፍስክ ዋጋ ተጨማሪ እሴት ታክስና ሰርቪስ ቻርጅ ጨምሮ ብር 444.66 እንደሚያቀርብ ይገልጻል፡፡በተጨማሪም አስተዳደሩ በአነስተኛ ዋጋ ሰራተኞችን እና እንግዶችን ለማስተናገድ የካፍቴርያ አገልግሎት እንዲሰጥ የውሃ፣ መብራት፣ የቤት ኪራይ ወጪን በነጻ በመሸፈን አንደኛ ደረጃ ብፌ የፍስክ ተጨማሪ እሴት ታክስ ጋር ብር 690.00 እንዲያቀርብ ከጎጆ ኢትዮጲያ ምግብ ቤት በቀን 15/07/2013 ውሉ የያዘ ቢሆንም አስተዳደሩ አንደኛ ደረጃ ብፌ እና የሪፍሬሽመንት አገልግሎት አነስተኛ ዋጋ ካቀረበለት ከጌት ፋም ሆቴል በብር 444.66 ግዥውን መፈፀም ሲገባው ከጎጆ ኢትዮጵያ ምግብ ቤት በብር 690.00 የሆቴል መስተንግዶ አገልግሎት ግዥ በማከናወን በድምሩ ብር 2,213,106.00 ብልጫ ክፍያ ተፈፅሞ መገኘቱ፤

6. <u>በማዕቀፍ ግዥ መፈጸም ሲገባው በዋጋ ማቅረቢያ በመግዛቱ በብልጫ የተከፈለ፤</u>

ሰኔ 2002 ዓ.ም በወጣው የፌዴራል መንግሥት የግዥ አፈፃፀም መመሪያ አንቀጽ 27/9 ከሀ እስከ ሠ በተዘረዘሩት ምክንያቶች ካልሆነ በስተቀር የመንግሥት መ/ቤቶች የማዕቀፍ ግዥን በመሰረዝ ከሌላ አቅራቢ ግዥ መፈፀም እንደሌለባቸው እና በአንቀጽ 27/10 የመንግሥት መ/ቤቶች የማዕቀፍ ስምምነት ቅጂ በመጠቀም በውሉ ላይ የተገለፁትን አቅርቦቶች ለመግዛት የሚያስችል የግዥ ትዕዛዝ ለማዕቀፍ ስምምነት አቅራቢው በማስተላለፍ እና አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ከአቅራቢው ጋር ተጨማሪ ውል በመፈፀም ግዥ ማከናወን እንደሚገባቸው ያዛል፡፡ አስተዳሩ በመመሪያ ተከትሎ ግዥ መፈጸሙን ለማረጋገጥ የግዥ ወጪዎች ናሙና ተወስዶ ኦዲት ሲደረግ፡-

☞ አስተዳድሩ በቀን 08/06/14 በባንክ ወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 289557 በብር 288,152.63 የወረቀት ግዥ በማከናወን ክፍያ ሲፈጽም የመንግስት ግዥና ንብረት ማስወገድ አገልግሎት በማእቀፍ ስምምነት ግዥ እንዲፈጸም ከላከው ዝርዝር ውስጥ የፕሪንተርና ፎቶ ኮፒ ወረቀት(Printer photocopy paper A4 size) ተጨማሪ እሴት ታክስን ጨምሮ በብር 323.07 ከአማ ወረቀትና የወረቀት ማሸጊያ አምራች ኃ/የተ/የግ/ማህበር ግዥ መፈጸም ሲገባው በዝርዝር ውስጥ ከሌለ ከሳይክሎፕስ አስመጪ ድርጅት በዋጋ ማወዳደሪያ የግዥ ዘዴ የአንዱን ዋጋ በብር 384.20 ግዥ በመፈጸሙ ልዩነት በብልጫ ብር 61.13፤ የገባው ወረቀት ብዛት በደስጣ 750 በመሆኑ በድምሩ ብር 45,847.50 መንግስትን ለተጨማሪ ወጪ የዳረገ መሆኑ፤

በኦዲት ታውቋል፡፡

ከላይ ከተራ ቁጥር 1 እስከ 6 በዝርዝር በተገለጹት ምክንያቶች በእኛ አስተያየት የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት አስተዳደር የሂሣብ ሪፖርቶች በበጀት ዓመቱ እስከ ሰኔ 30 ቀን 2014 ዓ.ም ድረስ የተሰበሰበው ገቢ የተፈጸመው ወጪና የበጀት አጠቃቀሙ በአጥጋቢ ሁኔታ አያሳዩም፡፡

ትኩረት የሚሹ ጉዳዮች (Emphasis matter)፤

1. **ቁጠባን፣ የአፈጻጸም ብቃትን እና ውጤታማነትን ማረጋገጥ ያላስቻለ ግዥ በተመለከተ፤**

የፌደራል መንግስት ግዥ አፈጻጸም መመሪያ ሰኔ 2002 በወጣው ክፍል አንድ አንቀጽ 4 ፊደል ሀ በግዥ አፈጻጸም ረገድ ገንዘብ ሊያስገኝ የሚችለውን ጥቅም ማስገኘት እንደሚገባ ይህም ማለት ቁጠባን ፣የአፈጻጸም ብቃትን እና ውጤታማነትን ማረጋገጥ እንዳለበት መመሪያው ይገልፃል፡፡ ይሁን እንጂ ፡- አስተዳደሩ በቀን 05/07/2013 ጨረታ ቁጥር 03/2013 የሚኒባስ ተሽከርካሪ ኪራይ እና 01/2013 አውቶሞቢል የተሽከርካሪ ለሰራተኞች እንዲያገለግሉ ኪራይ ሲፈጽም፣ በጨረታ ሰነድ ላይ ወደ አስተዳደሩ በኪራይ ለሚገቡ ሚኒባሶች እና አውቶሞቢል የቴክኒክ መመዘኛ መስፈርቶች ውስጥ ለሚኒባስ በአንድ ሊትር 9 ኪ.ሜ እና ለአውቶሞቢል በአንድ ሊትር 10 ኪ.ሜና ከዛ በላይ መጓዝ የሚችል መሆን እንዳለባቸው ቢገልጽም ተወዳዳሪዎች ያቀረቧቸው ተሽከርካሪዎች በሊትር ምን ያህል ኪሎ ሜትር መጓዝ እንደሚችሉ በአስተዳደሩ ሳይረጋገጥ ስራ ላይ እንዲውሉ በማድረግ በበጀት ዓመቱ በድምሩ ብር 42,765,935.24 ክፍያ ተፈጽሞ ተገኝቷል፡፡

2. **ሂሳብ መደቡን ያልጠበቀ የሌተር ኦፍ ክሬዲት በተመለከተ፤**

የፌዴራል መንግሥት የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ሰኔ 2003 ዓ/ም በወጣው መመሪያ ቁጥር 5 አንቀጽ 8 በተ.ቁ 7 ቁጥር በፊደል "ሀ" የመንግስት መ/ቤቶች የተፈቀደላቸውን በጀት በሥራ ክፍል ወይም በፕሮጀክት በፋይናንስ ምንጭ እና በየወጪ የሂሳቡ መደቡ የበጀት መቆጣጠሪያ ሌጀር ከፍተው እንቅስቃሴውን መመዝገብ፣ መቆጣጠር እና በበጀት አደረጃጀት ሥርዓት መሠረት የተፈቀደላቸውን በጀትና የወጣውን ወጪ ማሳየት እንዲቻል ተለይቶ በተሰጧቸው የበጀት መለያ መደቦች ተጠቅመው የሂሳብ እንቅስቃሴአቸውን መመዝገብ እንዳለባቸው ይገልጻል። ይሁን እንጂ አስተዳደሩ ሌተር ኦፍ ክሬዲት ከፍቶ ወደ ድርጅቶቹ የተላለፈ ገንዘብ የከፈተባቸውን ሂሳቦች በድርጅቶቹ ስም ለእቃ አቅራቢዎች ቅድመ ክፍያ (4253) መመዝገብ ሲገባው ለግዥ ሰራተኞች ቅድመ ክፍያ (4211) በማድረግ የተመዘገበ በመሆኑ በድምሩ ብር 223,808,202.76 ያለአግባብ የተመዘገበ መሆኖ ተገኝቷል፡፡

3. **ርክክብ ያልተደረገ ህንፃ በተመለከተ፤**

የህንፃ መመሪያ ቁጥር 5/2013 ክፍል ሁለት አስተዳደርና ማመልከቻ ቁጥር 19 የህንፃ መጠቀሚያ ፈቃድ 19.1 በምድብ "ሐ" ስር ለሚካተቱ ህንፃዎች የግንባታ ሥራው ሲጠናቀቅ የሕንፃ መጠቀሚያ ፈቃድ ማመልከቻ በቅጽ 018 መሠረት ተሞልቶ መቅረብ ይኖርበታል፣ በ19.2 ላይ የማመልከቻው ቅፅ በሕንፃው ባለቤት ወይም በህጋዊ ወኪል ወይም የመንግሥታዊ ወይም መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ንብረት ከሆነ በድርጅቱ የበላይ ኃላፊ ተፈርሞና ማህተም ተደርጎ መቅረብ አለበት፣ 19.3 ከማመልከቻው ቅፅ ጋር ተያይዘው መቅረብ ያለባቸው ሰነዶች፣ 19.3.1. ለአዲስ ግንባታ፣

ሀ) የግንባታ ፈቃድ

ለ) የግንባታ ማስጀመሪያ ሠነድ

ሐ) ግንባታው መጠናቀቁን የሚያረጋግጥ አማካሪ መሐንዲስና የሕንፃው ባለቤት የተፈራረሙበት የርክክብ ሠነድ፣

መ) የፕላን ማሻሻል ወይም ለውጥ ከተደረገ የተሻሻለውን አካቶ የተዘጋጀ ወይም የተከለሰ ፕላን ቅጂ፣

ሠ) በክትትልና ቁጥጥር ስለማለፉ ከፋይሉ ጋር የሚቀርቡ ሠነዶች ለክትትልና ቁጥጥር የአገልግሎት ክፍያ የከፈለበት ደረሠኝ ተያይዞ መቅረብ እንዳለበት ይገለጻል፡፡ በዚህ መሰረት እየተጠቀሙበት ያለው ሕንፃ የመጠቀሚያ ፈቃድ አግኝተው እደሆነ የገቡበት ለማረጋገጥ ኦዲት ሲከናወን፡-

አስተዳደሩ እየተጠቀመበት ያለው ህንፃ ግንባታን እያስገነባ የሚገኘው ኮንስትራክሽ ሚኒስቴር ግንባታውን እያከናወነ ያለው ደግሞ መከላከያ ሚኒስቴር እና የሚቆጣጠረው ደግሞ ኤም ኤች አማካሪ ሲሆኑ አስተዳደሩ ወደ ህንፃው ሲገባ ርክክብ ያደረገበት ማስረጃ ካለ የተጠየቀ ቢሆንም ምንም አይነት ርክክብ ያልተደረገ መሆኑ እና አስተዳደሩ ርክክብ ባላደረገበት ሁኔታ ህንፃው መጠቀም ከጀመረበት ጊዜ ጀምሮ የተለያዩ ሥራዎችን ህንፃው ላይ እያከናወነ መሆኑ፡- ለምሳሌ የፓርቲሽን ስራ፣ኢንቴርየር ዲዛይን ሥራ፣ ቢዝመንትቶች ላይ የማፍረስና እንደገና የመስራት እና ሌሎችም ርክክብ ባልተደረገበት ሁኔታ ስራዎች እየተሰሩ በኦዲት ታውቋል፡፡

ሌሎች ጉዳዮች (Other Matters)

1. **የንብረት አመዘጋገብ፣ አያያዝ እና አጠባበቅን በተመለከተ፤**

የፌዴራል መንግሥት ንብረት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 9/2003 አንቀጽ 10 ፊደል ሀ መሠረት የመ/ቤቶች የስቶክ መዛግብቶች የመያዝና ስቶክ የመረከብ እንዲሁም ወጪ የማድረግ ኃላፊነቶች ለአንድ ሠራተኛ መሰጠት እንደሌለባቸው እና በዚህ የሥራ መደብ ላይ የሚገኙ ሠራተኞች መካከል በቂ የኃላፊነት መነጣጠል መደረጉን ማረጋገጥ እንዳለባቸው ይገልጻል፡፡ በዚሁ መመሪያ አንቀጽ 10/5 የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች በእጃቸው ያለውን የመንግሥት ንብረት በጥንቃቄ የመያዝ፤ የመጠቀም፤ የመቆጣጠር እና አገልግሎቱ ሲያበቃ ወይም አገልግሎቱ ላይ በማይውሉበት ጊዜ በወቅቱ በተገቢው መንገድ እንደሚወገዱ ይገልጻል፡፡ አስተዳደሩ የንብረት አመዘጋገብ፣ አያያዝ እና አጠባበቅ በመመሪያው መሰረት እያከናወነ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡-

- ብዛት ያላቸው ብረታ ብረቶች፤ የቴሌ ጥቅል ገመዶች እና ሁለት የዳታ ሴንተር ማቀዝቀዣዎች ሳርቤት በሚገኘው የአስተዳድሩ ቅጥር ግቢ ውስጥ ለፀሀይና ለዝናብ በተጋለጠ ቦታ ለረጅም ጊዜ ተቀምጠው መገኘታቸው፤
- ብዛታቸው 19 የሚሆኑ ኮንቴይነሮች ዲጂታል ቴሌቭዥን ግዥ ተፈጽሞባቸው ከውጪ የመጡ እና ረዘም ላሉ ጊዜያቶች ርክክብ ሳይፈፀም ተቀምጠው የሚገኙ ከመሆኑም በተጨማሪ በየቀኑ የኮንቴይነር ክራይ ክፍያ የተፈፀመባቸው ሲሆን ለተገዙበት ዓላማ ሳይውሉ ሳርቤት በሚገኘው የአስተዳድሩ ቅጥር ግቢ ውስጥ ተቀምጠው የሚገኙ መሆኑ፤
- ሁሉም ንብረት ክፍሎች ውስጥ ቢን ካርድ የሌለ መሆኑ፤
- የስቶክ ካርድ ምዝገባ የሚያከናውኑ ባለሙያዎች ቢኖሩም ምዝገባው የሚከናወነው በኤክስኤል ሶፍት ዌር በመሆኑ ለቁጥጥር አመቺ አለመሆኑ፤
- የንብረት ክፍሎቹን ቁልፍ መያዝ ያለበት ንብረት የመጠበቅ ኃላፊነት ባለበት ሰው መሆን ሲገባው የእስቶክ አስተዳደር ቡድን መሪው የንብረት ክፍሎቹን ቁልፍ ይዞ የሚገኝ መሆኑ፤

- ☞ አስተዳደሩ ያሉት ንብረት ክፍሎች ንብረቶችን ለማስቀመጥ ምቹ ባልሆነ በቆርቆሮ የተሰሩ ሲሆን ንብረቶቹ በሙቀትና ቅዝቃዜ ምክንያት ለብልሽት እየተጋለጠ መሆኑ፤
- ☞ የመለዋወጫ ዕቃ ንብረት ክፍል እና የኮንስትራክሽን ንብረት ክፍል ቆጠራ የተደረገ ቢሆንም በቆጠራ የተገኘው እና በንብረት ክፍል ውስጥ ያለው ንብረት ልዩነት የሚያሳይ (ቆጠራው ውስጥ ያልተካተቱ ንብረቶች) የሚገኙ መሆኑ፤

<u>አላቂ እና ቋሚ ዕቃ ንብረት ክፍል በተመለከተ</u>

- ☞ ብዛታቸው 16 ቴኪ ፍሊት ፀረ ነፈሳት እና ብዛቱ 160 የመስታወት ማዕጃ የአገልግሎት ጊዜያቸው ያለፈ ሆኖ ሳለ በንብረት ክፍል ውስጥ መወገድ ሲገባው ሳይወገዱ አገልግሎት ከሚሰጡት ጋር ተቀምጠው መገኘታቸው፤
- ☞ የተለያዩ ህትመቶች አገልግሎት ሣይሰጡ ተቀምጠው የሚገኙ መሆናቸው፤
- ☞ አላቂ እና ቋሚ ንብረት በአንድ እስቶር ተቀላቅለው የተቀመጡ መሆናቸው፤

<u>ያገለገሉ ተመላሽ ንብረት ክፍል በተመለከተ</u>

- ☞ ብዛት ያላቸው የኤሌክትሮኒክስ ዕቃዎች፣ የመኪና ጎማዎች፤ የመኪና መለዋወጫዎች፤ ቶነሮች፣ ፈርኒቸሮች በመ/ቤቱ ግምጃ ቤት ውስጥ ለቁጥጥር በማይመች መልኩ ተቀምጠው የሚገኙ መሆኑ፤
- ☞ ያገለገሉ በርከት ያሉ የመኪና ጎማዎች፣ የመኪና መለዋወጫ እስፔር ፓርቶች እና በርሜሎች እርምጃ ሳይወሰድባቸው ስቶሩ አጣበው የሚገኙ መሆኑ፤
- ☞ ንብረቶች ወደ ተመላሽ ንብረት ክፍል ተመልሰው ከመግባታቸው በፊት ፍተሻ መደረግ ሲገባው ከገቡ በኋላ ፍተሻ የሚደረግላቸው መሆኑ፤
- ☞ ተመላሽ ንብረት ክፍል ውስጥ አዲስ ዕቃዎች የሚገኙ መሆኑ፤

  በኦዲት ታውቋል፡፡

<u>የተሽከርካሪዎች አስተዳደር በተመለከተ</u>

የፌደራል መንግስት የተሽከርካሪዎች ስምሪት እና አጠቃቀም መመሪያ ቁጥር 32/2004 አንቀጽ 6 ንኡስ አንቀጽ 3 ላይ እያንዳንዱ ተሽከርካሪ ርክክብ ከተፈጸመበት ጊዜ ጀምሮ እስኪወገድ ድረስ በኪሎ ሜትር የሚጠቀመውን የነዳጅ፤ ዘይት፤ እና ቅባት ፍጆታ መጠን፤ የጥገና ወጪ፤ የተጓዘው ኪ/ሜ መጠን በእነማን ስር እንደነበር ....ወዘተ እና ሌሎችንም አካቶ መያዝ እንዳለበት ይገልጻል፡፡ በተጨማሪም የፌደራል መንግስት ንብረት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 9/2003

ክፍል 4 አንቀጽ 20 ከተራ ቁጥር1-2 በተመለከተው መሰረት የመንግስት ንብረት ኢኮኖሚያዊና ውጤታማ በሆነ መንገድ አገልግሎት እንዲሰጥ ተገቢው ጥገናና እንክብካቤ የሚደረግለት መሆኑን እና በዚሁ መመሪያ አንቀጽ 20 ተራ ቁጥር 1 ከፊደል ሀ-መ በተዘረዘሩት ምክንያቶች ሊወገዱ የሚገባቸው ንብረቶች እንዲወገዱ መደረግ እንደሚገባቸው ይገልፃል፡፡ አስተዳደሩ የተሽከርካሪ አያያዝና አጠቃቀም በመመሪያው መሰረት ተግባረዊ እያደረገ መሆኑን ለማረጋጥ ኦዲት ሲደረግ፡-

- በአስተዳድሩ የሚገኙ 136 ተሽከርካሪዎቹ በአንድ ሊትር ነዳጅ ምን ያህል ኪሎ ሜትር እንደሚጓዙ /normalization/ ከተሰራላቸው ሦስተ ዓመታት ያለፋቸው በመሆኑ ተሽከርካሪዎቹ የተጠቀሙት ነዳጅ እና መጠቀም የነበረባቸውን ነዳጅ በኦዲት ንጽጽር ማድረግ ያልተቻለ መሆኑ፡፡
- ሁለት ተሽከርካሪዎች የሰሌዳ ቁጥር ድርብ ተግባር ኢት 4-13651፤ የጭነት የሰሌዳ ቁጥር ኢት 4-13301፤ የነዳጅ መቆጣጠሪያ ጌጃቸው የማይሰራ መሆኑ፤
- በአስተዳድሩ ጋራዥ ውስጥ ብዛታቸው 13 ተሽከርካሪዎች ከስድስት ወር እስከ ሁለት አመት በላይ ተበላሽተው ለጥገና የቆሙ አስራ ሁለት ተሽከርካሪዎች ያሉ መሆኑ፤

  በኦዲት ታውቋል፡፡

2. <u>የካፍቴሪያ አገልግሎት ግዥን በተመለከተ፤</u>

የተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅን ለማሻሻል የወጣ አዋጅ 609/2002 አንቀጽ 22 ንኡስ አንቀጽ 1 በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ /6/ እና /7/ በሌላ ሁኔታ ካልተወሰነ በስተቀር ለተጨማሪ እሴት ታክስ የተመዘገበና ታክስ የሚከፈልበት ግብይት የሚያካሂድ ሰው ደረሰኝ ወዲያውኑ መስጠት አለበት፡፡ ለተጨማሪ እሴት ታክስ ያልተመዘገበ ሰው የተጨማሪ እሴት ታክስ ደረሰኝ መስጠት እንደማይቻል እንዲሁም የኢትዮጲያ ፌደራል መንግስት ግዥ እና ንብረት አስተዳደር በአዋጁ አንቀጽ 61 ንኡስ አንቀጽ 4 የማዕቀፍ ስምምነት የሚፈጸመው በግልጽ ጨረታ የግዥ ዘዴ ሆኖ፣ እስከ ሦስት አመት ድረስ ጸንቶ ሊቆይ ይችላል በማለት ደንግጓል፡፡ አስተዳደሩ በመመሪያው መሰረት ግዥዎችንና ክፍያዎችን እያከናወነ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲከናወን፡- በቀን 15/07/2013 ከነጆ ኢትዮጲያ ምግብ

ቤት ጋር የካፍቴሪያ አገልግሎት ግዥ ለማቅረብ የተደረገ ውል የተፈራረመ ሲሆን በግዥ ሂደቱ፣ በውሉ እንዲሁም በአቅርቦቱ ላይ የታዩ ክፍተቶች እንደሚከተለው ቀርበዋል፤-

- ☞ ምግብ ቤቱ በውሉ ላይ የሚያቀርባቸው ምግቦች ዋጋ ከነተጨማሪ እሴት ታክሱ መሆኑን ቢገልጽም እንዲሁም ለአስተዳደሩ የሚያቀርባቸው የሽያጭ አገልግሎቶች ላይ ተጨማሪ እሴት ታክስ (VAT) ደረሰኝ የሚቆርጥ ሲሆን ፤ ለተጠቃሚዎች ሽያጭ ሲያከናውን የተጨማሪ እሴት ታክስ (VAT) ደረሰኝ የማይቆረጥ መሆኑ፤

በውል ክፍል ስምንት ልዩ የውል ሁኔታዎች ፊደል ሐ የግዥ ፈጻሚው አካል ግዴታዎች በሚለው አርዕስት ስር

- ☞ የውል ጊዜው ውሉ ከተፈረመበት ቀን ጀምሮ ለ7 ዓመታት ሆኖ እንደ አስፈላጊነቱ የሚራዘም ይሆናል በማለት በአዋጁ ከተቀመጠው የ3 አመት የጊዜ ገደብ በላይ ውል የተሰጠ መሆኑ፤
- ☞ የአስተዳደሩ የጠቅላላ አገልግሎት ስራ አመራር ዳሬክቶሬት አገልግሎት አሰጣጥና ሌሎች ጉዳዮች በቅርበት እንደ ሚከታተል የተገለፀ ቢሆንም ክፍሉም ይህን ጉዳይ ተከታትሎ ምግብ ቤቱ ተጨማሪ እሴት ታክስ ደረሰኝ ማስቆረጥ ማስጀመር የነበረበት ቢሆንም ያላደረገ መሆኑ፤

በአጠቃላይ ጎጆ ኢትዮጵያ የግዥ እና የተጨማሪ እሴት ታክስ መመሪያን ሳይጠብቅ ውሉን ከፈረመበት 15/07/2013 ጀምሮ ከተጠቃሚዎች የሚሰበስበውን ተጨማሪ እሴት ታክስ ለሚመለከተው ገቢ ሰብሳቢ ተቋም ገቢ ሳያደርግ አቅርቦትም እየፈጸመ ያለ መሆኑ ታውቋል፡፡

3. <u>የውስጥ ኦዲት ሪፖርት በተመለከተ፤</u>

የፌደራል መንግሥት የውስጥ ኦዲት መመሪያ ቁጥር 7/2003 ክፍል አምስት የውስጥ ኦዲት ዕቅድና ሪፖርት ማቅረቢያ የጊዜ ሰሌዳ ከዕቅዱ ጋር የተገናዘበ የውስጥ ኦዲት ሪፖርት ውጤቱ በኦዲት የሪፖርት አጻጻፍ ሥነ ሥርዓት መሠረት ደረጃውን ጠብቆ ተዘጋጅቶ መቅረብ አለበት፤ የውስጥ ኦዲት የሥራ ክፍሉ ባዘጋጀው ዕቅድ መሰረት በየሩብ ዓመቱ ባከናወነው ኦዲት የደረሰበትን ውጤት በኦዲት ዕቅዱ መሰረት የመጀመሪያው ሩብ ዓመት እስከ ጥቅምት 30፣ የሁለተኛው

ሩብ ዓመት እስከ ጥር 30፣ የሦሥተኛው ሩብ ዓመት እሰከ ሚያዚያ 30 እንዲሁም የአራተኛው ሩብ ዓመት እስከ ነሐሴ 15 ድረስ መሆን ይኖርበታል በማለት ይደነግጋል፡፡ በዚህ መሰረት ኦዲት ሲከናወን፡-

- ☞ በስራ ክፍሉ መዋቅር መሰረት 11 የሰው ሃይል እንደሚያስፈልገው የተገለጸ ቢሆንም አሁን የስራ ክፍሉ 6 የሰው ሃይል ብቻ ያለው በመሆኑ ቀሪው 5 የስራ መደብ ያልተሸፈነ መሆኑ፣
- ☞ ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ባወጣው ሪፖርት ማቅረቢያ የጊዜ ሰሌዳ ማለትም የመጀመሪያው ሩብ አመት ሪፖርት እስከ ጥቅምት 30 ድረስ፣ የሁለተኛዉ ሩብ አመት እስከ ጥር 30 ድረስ፣ የሶስተኛዉ ሩብ አመት ሪፖርት እስከ ሚያዚያ 30 እንዲሁም የአራተኛ ሩብ አመት ሪፖርት እስከ ነሐሴ 15 ድረስ ለማከናወን ያቀደ ቢሆንም የመጀመሪያው ሩብ አመት ሪፖርት ጥር /2014፣ የሁለተኛዉ ሩብ አመት ሪፖርት መጋቢት/2014፣ የሶስተኛዉ ሩብ አመት ሰኔ/2014 የዕቅድ ጊዜውን ጠብቆ ያላከናወነ መሆኑ በኦዲት ታውቋል፡፡

የህግ ጉዳዮች በተመለከተ (Compliance Issue)፣

1. ለሶስተኛ ወገን የተሰጠ የጽዳት አገልግሎትን በተመለከተ፤

የፌዴራል የመንግስት ሰራተኞች አዋጅ ቁ.1064/2010 አንቀጽ 22/1 አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ማንኛውም መ/ቤት ሚኒስቴሩን በማስፈቀድ የህዝብን ጥቅም በማይጎዱ የተወሰኑ የስራ መደቦችን ወይም ሥራዎችን ለግል ድርጅቶች ወይም ለሌሎች ተቋማት በውል በማሸጋገር እንዲሰሩ ማድረግ እንደሚቻል ይደነግጋል፡፡ እንዲሁም የፌደራል መንግስት ግዥ አፈጻጸም መመሪያ ሰኔ 2002 በወጣው ክፍል አንድ አንቀጽ 4 ፊደል ሀ በግዥ አፈጻጸም ረገድ ገንዘብ ሊያስገኝ የሚችለውን ጥቅም ማስገኘት እንደሚገባ ይህም ማለት ቁጠባን፣ የአፈጻጸም ብቃትን እና ውጤታማነትን ማረጋገጥ እንዳለበት ይገልጻል፡፡ አስተዳደሩ ለሶስተኛ ወገን የሚሰጡ ስራዎችን በመመሪያው መሰረት እያከናወነ መሆኑን ለማረጋገጥ የአገልግሎት ግዥ ወጪዎች ናሙና ተወስዶ ኦዲት ሲደረግ፡-

አስተዳደሩ ጽዳት አገልግሎት ግዥ በግልጽ ጨረታ ተወዳድሮ ካሸነፈው ከሸበሌ የጽዳት ስራዎች ድርጅት በቀን 30/07/2013 ዓ.ም በውል

ቁጥኢ.መደኤ/ውዝአቡ2013/ከቁ.0072 ብር 27,158,400.00 ውል የተፈራረመ ቢሆንም፡-

- ስራዎቹ ለሶስተኛ ወገን ከመሰጠቱ በፊት ከሰው ሃይል እና ከመንግስት ውስን ሃብት አኳያ የአዋጭነት ጥናት ሳይደረግና በመመሪው መሰረት ስራዎቹን ለሶስተኛ ወገን ለማሸጋገር ሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን ሳይጠየቅና ሳያስፈቅድ ለሶስተኛ ወገን የተሰጡ በመሆኑ፣ በድምሩ ብር 9,408,078.14 የግዥ ሂደቱን ሳይከተል የጽዳት አገልግሎቱን ግዥን ከሶስተኛ ወገን በማከናወን ክፍያ ተፍጽሞ ተገኝቷል፡፡

2. <u>በወቅቱ ያልተወራረደ ውዝፍ ተሰብሳቢ ሂሳብ፤</u>

በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 190/2002 አንቀጽ 32 እንዲሁም በፌዴራል መንግሥት መሥሪያ ቤቶች የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 መሰረት ለግዥ የተሰጠ ቅድሚያ ክፍያ በሰባት ቀናት ውስጥ፤ በመመሪያ ቁጥር 4/2003 መሰረት ደግሞ ለውሎ አበልና ለመጓጓዣ የተሰጠ ቅድሚያ ክፍያ ሰራተኛው ሥራውን አጠናቆ ከተመለሰ በኋላ በሰባት ቀናት ውስጥ መወራረድ እንዳለበት ያዛል። ይሁንና አስተዳደሩ ተሰብሳቢ ሂሳቦችን በደንቡና በመመሪያው መሰረት በወቅቱ እንዲወራረዱ የሚያደርግ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡ ከመደበኛ ሂሳብ ብር 214,041,229.11 እና ከፕሮጀክት ብር 753,248.34 በድምሩ ብር 214,794,477.45 ከሚታየው ውስጥ ብር 214,777,791.24 ከ1 ወር እስከ 10 እና ብር 16,686.21 ከ10 ዓመት በላይ በወቅቱ ያልተወራረደ ውዝፍ በተሰብሳቢ ሂሳብ መኖሩ በኦዲት ታውቋል፡፡

3. <u>ግዥዎች ሲከናወኑ ገዳቢ የሆነ መስፈርት መውጣቱን በተመለከተ፤</u>

የፌደራል መንግሥት የግዥ አፈጻጸም መመሪያ ሰኔ 2002 አንቀጽ 4 ፊደል ‹‹ረ›› በአዋጅ እና በዚህ መመሪያ በተፈቀደው ልዩ አስተያየት መሰረት የሀገሪቱን ኢኮኖሚ የሚደግፍ የሀገር ውስጥ አምራቾችን፣ ኩባንያዎችን እና አነስተኛ ጥቃቅን ኢንዱስትሪዎችን ማበረታታት፡ እንዳለባቸው መመሪያው ይገልጻል፤ እንዲሁም የግዥ አፈጻጸም መመሪያ ቁጥር 3/2002 ጥቃቅን እና አነስተኛ ተቋሚት ለውድድር ሲቀርቡ በአዋጅ እና በመመሪያ በተፈቀደላቸው መብት መሰረት ካደራጃቸው ተቋም የዋስትና ደብዳቤ ካቀረቡ በቂ ሆኖ ሳለ በተጨማሪም የፌደራል

መንግስት ግዥ አፈጻጸም መመሪያ ሰኔ 2002 ክፍል አንድ አንቀጽ 4 ፊደል ሀ በግዥ አፈጻጸም ረገድ ገንዘብ ሊያስገኝ የሚችለውን ጥቅም ማስገኘት እንደሚገባ ይህም ማለት ቁጠባን፣ የአፈጻጸም ብቃትን እና ውጤታማነትን ማረጋገጥ እንዳለበት መመሪያው ይገልፃል፡፡ በዚህ መልኩ ግዥው እንደተፈጸመ ለማረጋገጥ ኦዲት ሲከናወን፡-

- አስተዳደሩ በ2014 በጀት ዓመት የጨረታ ማስታወቂያ ሲያወጣ ያደራጃቸው ተቋም የዋስትና ደብዳቤው ላይ የገንዘብ መጠን መግለጽ አለበት በሚል ዋስትና የሚጽፈው በቂ ሆኖ ሳለ የገንዘብ መጠን መጠቀስ አለበት በማለት ውድድሩን የሚሳተፉ አካላት ገዳቢ የሆነ እና በህግ የተፈቀደ መብትን የሚጥስ የማወዳደሪያ መስፈርት በጨረታ ሂደት ውስጥ የወጣ መሆኑ እና በዚህ መስፈርት ምክንያት ድርጅቶቹ ከውድድር ውድቅ የሚደረጉ መሆኑ፤
- የጨረታ ቁጥር 12 የህንፃ መሳሪያ ግዥ የጨረታ ዶክመንቱ ሲዘጋጅ እና ሲወጣ ተመሳሳይ የሆኑ ነገሮች ተሰብስበው መውጣት የነበረባቸው ቢሆንም ተበታትነው የወጡ መሆኑ ለምሳሌ ሚስማር፤
- ዕቃዎች ከጨረታ ከገበያ ጥናት አንፃር ተጋነዋል ተብለው ሲጣሉ ተጋነነ የሚለው መስፈርት ያልተቀመጠለት መሆኑ፤
- የጨረታ ሰነድ ቁጥር 8/2014 ግዥው አስፈላጊ መሆን አለመሆኑ ጨረታ ከመውጣቱ በፊት መጣራት የነበረበት ሆኖ ሳለ ጨረታ ከወጣ እና ውድድር ከተካሔደ በኋላ ዕቃዎቹ አስፈላጊ ስላልሆኑ በሚል ከውድድር ውጪ የሚደረጉ መሆኑ በኦዲት ታውቋል፡፡

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት